ማርች 22, 2022

የተወደዳችሁ የ Redland Middle School ት/ቤት ማህበረሰብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመጠጥ ውሃ ምርመራ ፕሮግራም በየሶስት አመቱ በትምህርቶች ያለውን ውሃ እንደገና ምርመራ የማድረግ አካል በመሆኑ፣ የት/ቤትዎ የመጠጥ ውኃ ምርመራ ተጠናቋል። የምርመራ ውጤቶች እንደሚያመለክቱት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የመጠጥ ውሃ ማሰራጫዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል እና በሜሪላንድ ትግበራ በቢሊየን (ppb) ደረጃ 5 ወይም ከዚያ በላይ የእርሳስ መጠን ክምችት (lead concentrations) ያለበት መሆኑን ተረጋግጧል። ዝርዝር ዘገባው በ MCPS የመጠጥ ውሃ የምርመራ ፕሮግራም ድረ ገጽ ላይ በሚከተለው ሊንክ ይገኛል።

http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/facilities/maintenance/services/water.aspx።

በሜሪላንድ የአካባቢ ጥበቃ ዲፓርትመንት ድንጋጌ መሠረት ከፍ ያለ የእርሳስ ክምችት ያላቸው ማሰራጫዎች ከአገልግሎት ተወግደዋል እናም በእነዚህ ማሰራጫዎች ላይ የማሻሻያ እቅድ ተግባራዊ ይደረጋል ። የማሻሻያው ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ የማስተካከያ እርምጃዎቹ ውጤታማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የውኃ ማሰራጫዎቹ እንደገና ምርመራ ይደረጋል። የተወሰኑ የማሻሻያ እርምጃዎች በድህረ ማገገሚያ ክትትል የምርመራ ሪፖርት ውስጥ ይካተታሉ።

በተጨማሪም በዚህ አመት ፍትሃዊ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማረጋገጥ እና የፕላስቲክ ብክለትን/ብክነትን ለመቀነስ እየተሰራ ነው። ከተጠናቀቀ በኋላ፣ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ቢያንስ በጠርሙስ ውሃ የሚቀዳበት ሁለት ጣቢያዎች ይኖራሉ። የውሃ ጠርሙሶች መሙያ ጣቢያዎች እርሳስን ለማስወገድ ማጣሪያ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጫ ይኖራቸዋል። የት/ቤትዎ ርእሰመምህር የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታን በተመለከተ ማሻሻያ ሊሰጡ ይችላሉ።

**ሰዎች ለእርሳስ የሚገላጡባቸው መንስኤዎች**

እርሳስ ያለበትን ቀለም (lead-based paint) ጨምሮ ሰው የሚጋለጥባቸው ብዙ የተለያዩ መንስኤዎች አሉ፤ በእርሳስ የተበከለ አቧራ ወይም አፈር፣ አንዳንድ የቧንቧ እቃዎች፣ የተወሰኑ የሸክላ ስራዎች፣ ፔውተር፣ የነሐስ እቃዎች፣ ምግቦች እና መዋቢያዎች፣ በሥራ ቦታ መጋለጥ፣ እና ከተወሰኑ የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ቦታዎች መጋለጥ ይኖራል። ከአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ (EPA) እንደተገለጸው፣ አንድ ሰው ለእርሳስ (lead) ሊጋለጥ ከሚችለው እስከ 20 በመቶ የሚደርሰው ከመጠጥ ውሃ ሊመጣ ይችላል፣ ለጨቅላ ህጻናት ደግሞ እርሳስ (lead) ያለበት ውሃ ጋር የተቀላቀለ ፎርሙላ ሲመገቡ ይህ ተጋላጭነት ከ 40 እስከ 60 በመቶ ሊጨምር ይችላል።

**ከመጠጥ ውሃ የእርሳስ ተጋላጭነትን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል**

- እርሳሱን ለማስወገድ ቀዝቃዛ ውሃ የተወሰነ ያህል እንዲፈስ ማድረግ፣ ውሃ ለብዙ ሰአታት ያልተጠቀሙበት/ያልፈሰሰ ከሆነ ካልዋለ ከ15 እስከ 30 ሰከንድ ወይም ቀዝቃዛ እስኪሆን ድረስ ውሃውን ለመጠጥ ወይም ለማብሰያ ከመጠቀምዎ በፊት ያፈስሱ።
- የሕፃን ፎርሙላ ለማብሰል እና ለማዘጋጀት ቀዝቃዛ ውሃ ይጠቀሙ። በቧንቧው የሚገኝ እርሳስ በሙቅ ውሃ በቀላሉ ይቀልጣል።
- እባክዎን ውሃውን ማፍላት የእርሳስ ክምችት መጠንን (lead levels) እንደማይቀንስ ያስተውሉ።

**ተጨማሪ መረጃ**

በቤትዎ/በመኖርያ ህንፃ ዙሪያ ለሊድ/ለእርሳስ መጋለጥን ለመቀነስ እና ሊድ/እርሳስ በጤንነት ላይ ስለሚያስከትላቸው ተፅእኖዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ www.epa.gov/lead የ EPA ድረገጽ ይጎብኙ። ስለ ተጋላጭነት የሚያሳስብዎት ከሆነ ልጅዎን የእርሳስ/ሊድ ምርመራ ለማድረግ እንዴት እንደሚችሉ ለማወቅ የጤና እንክብካቤ የሚሰጥዎትን የጤና ባለሙያ ያነጋግሩ።

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፣ እባክዎን የቡድን መሪ Mr. Brian A. Mullikin team leader, Division of Sustainability and Compliance፣በ 240-740-2324 ደውለው ያነጋግሩ ወይም በኢሜል Brian_A_Mullikin@mcpsmd.org ያግኙዋቸው።

ከልብ የሆነ

Lynne M. Zárate,
Director
Division of Sustainability and Compliance